# ታማኝ የሆኑ ጓደኞች ማግኘት የምትችለው እንዴት ነው?

***መመሪያ፦*** *ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።*

***ዋነኞቹ ባለ ታሪኮች፦*** *ዮናታን፣ ዳዊት እና ሳኦል*

***ታሪኩ በአጭሩ፦*** *ዳዊት ጎልያድን ከገደለ በኋላ ዮናታንና ዳዊት በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ሆኑ።*

**1** *ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—1 ሳሙኤል 17:57 እስከ 18:11ን፤ 19:1ን፤ 20:1-17, 41, 42ን አንብብ።*

ሳኦልን በአእምሮህ ስትስለው ምን ዓይነት ቁመና ያለው ሰው ይመስልሃል? (ፍንጭ፦ 1 ሳሙኤል 10:20-23ን ተመልከት።) ______________________________

______________________________

ዳዊት ከዮናታን ጋር ሲገናኝ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም። ታዲያ ዳዊትን በአእምሮህ ስትስለው ምን ዓይነት ቁመና ያለው ልጅ ይመስልሃል? (ፍንጭ፦ 1 ሳሙኤል 16:12, 13ን ተመልከት።) ______________________________

______________________________

በአንደኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 20 ወደ መጨረሻው አካባቢ ተመዝግቦ እንደሚገኘው ዳዊትና ዮናታን ሲሰነባበቱ ስሜታቸውን እንዴት የገለጹ ይመስልሃል? ______________________________

______________________________

______________________________

**2** *ጥልቅ ምርምር አድርግ።*

ታሪኩ "የዮናታን ነፍስ ከዳዊት ነፍስ ጋር ተቈራኘች" ይላል። *ኮንቴምፖራሪ ኢንግሊሽ ቨርዥን* ይህን ጥቅስ "ዳዊትና ዮናታን በጣም የሚዋደዱ ጓደኛሞች ሆኑ" በማለት አስቀምጦታል። (1 ሳሙኤል 18:1) ዮናታን ዳዊትን የወደደው ዳዊት ምን ዓይነት ባሕርያት ስላሉት ሊሆን ይችላል? (ፍንጭ፦ 1 ሳሙኤል 17:45, 46ን ተመልከት።) ______________________________

______________________________

______________________________

ዳዊትና ዮናታን በመካከላቸው በግምት የ30 ዓመት ልዩነት አላቸው። በመካከላቸው የዕድሜ ልዩነት

ቢኖርም "በጣም የሚዋደዱ ጓደኞሞች" እንዲሆኑ የረዳቸው ምን ይመስልሃል? ______

በጣም ደስ ከሚለው ከዚህ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው እውነተኛ ጓደኞሞች ሊኖሯቸው የሚገቡት አንዳንድ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? (ፍንጭ፦ ምሳሌ 17:17ን እና 18:24ን ተመልከት።) ______

ዮናታን ከገዛ አባቱ ይልቅ ለዳዊት ታማኝ የሆነው ለምንድን ነው? ______

❸ ***ከዚህ ታሪክ ያገኘሽውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ። ከዚህ በታች ስለተዘረዘሩት ነገሮች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦***

ጓደኝነት። ______

ታማኝነት። ______

በዕድሜ ከሚበልጡን ሰዎች ጋር ጓደኝነት መመሥረት። ______

በጣም ጥሩ ጓደኛ ለማግኘት ምን ማድረግ ትችላለህ? ______

❹ ***ከዚህ ታሪክ ውስጥ ይበልጥ ትምህርት ያገኘህበት ሐሳብ የትኛው ነው? ለምን እንዲህ አልክ?***

______



www.jw.org © 2010 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania